https://chilot.me

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 4/2012

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 124 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የመራጮች ትምህርት ስለሚሰጡ አካላት፣ ትምህርቱ ስለሚሰጥበት አሠራር እና ለነዚህ አካላት የማስተማር ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነምግባር ለመደንገግ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና የስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 04/2012 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. “የምርጫ ሕግ” ማለት የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁ. 1162/2011 ነው።
2. “ቦርድ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3. “ክልል” ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል።
4. “አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት” ወይም “ድርጅት” ማለት ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ኢትዮጵያውያን በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ የመንግሥት አካል ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ሕጋዊ ዓላማን ለማሳካት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ሲሆን፣ የሙያ ማኅበራትን፤ የብዙኃን ማህበራትን እና የድርጅቶች ኅብረቶችን ይጨምራል።
5. “የምርጫ አስፈጻሚ” ማለት በየደረጃው ምርጫን ለማስፈፀም በቦርዱ የሚመደብ ሰው ነው።

6. "የፖለቲካ ድርጅት" ወይም "የፖለቲካ ፓርቲ" ማለት ዜጎች ተደራጅተው የሚመሠርቱት የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ ደረጃ በምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በምርጫ ህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው።
7. "የመራጮች ትምህርት" ማለት ዜጎች የምርጫን ጠቀሜታና አስፈላጊነት ተገንዝበው በፍላጎትና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እንዲሁም በምርጫው ሂደት ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን በቂ መረጃ የሚያገኙበት ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ መንገድ የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ነው።
8. "የትምህርት ተቋም" ወይም "ተቋም" ማለት ስልጣን ባለው አካል የእውቅና ፈቃድ የተሰጠው ዩኒቨርሲቲ፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ ወይም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ማለት ነው።
9. "አሰልጣኝ" ማለት የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ በቦርዱ የተሰጠው ድርጅት የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ ለቦርዱ አሳውቆ የሚያሰማራው ግለሰብ ነው።
10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ድርጅት ነው።

**አንቀጽ 3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ በምርጫ ህጉ መሠረት በሚካሄድ በማንኛውም ምርጫ ወይም ህዝበ ውሳኔ ዙሪያ የመራጮች ትምህርት በሚሠጡ የሀገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የትምህርት ተቋማት እና አሰልጣኞቻቸው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 4. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በሴት ፆታ የተደነገገው የወንድንም ፆታ ያካትታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

## ምዕራፍ ሁለት
## የመራጮች ትምህርት ስለመስጠት

### አንቀጽ 5. የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት

1. በምርጫ ህጉ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት የቦርዱ ነው።
2. ቦርዱ መራጮች በቂ ምርጫ ነክ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የመራጮች ትምህርት ይሰጣል።
3. ቦርዱ የመራጮች ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የትምህርት ተቋማት፤ የማስተማር ፈቃድ ይሰጣል።
4. በአዋጁ መሠረት በቦርዱም ሆነ በቦርዱ ፈቃድ በሚሰጣቸው ተቋማትና ድርጅቶች የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ቦርዱ ከሲቪል ማህበራት ጋር በመመካከር የሚያዘጋጀው የማስተማሪያ ሰነዶችን መሠረት ያደረገ ይሆናል።
5. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቦርዱ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት ፈቃድ ከተሰጣቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ተቋማት ጋር በመተባበር የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
6. ማንኛውም ሰው ያለቦርዱ ፈቃድ የመራጮች ትምህርትና መረጃ መስጠት አይችልም። ያለ ፈቃድ የመራጮች ትምህርት በሚሰጥ ማንኛውም ሰው ላይ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### አንቀጽ 6. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት

1. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 በሚያደርገው ክትትል እና ቁጥጥር የቦርዱ ፈቃድ ሳይኖረው የመራጮች ትምህርት የሚሰጥ ድርጅት ወይም ተቋም መኖሩን እራሱ በሚያደርገው ማጣራት ወይም በሚደርሰው ጥቆማ መሰረት ያረጋገጠ

እንደሆነ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ የማስተማር ፈቃድ በቦርዱ እንዲሰጠው እንዲያመለክት በደብዳቤ ያሳውቀዋል፤ የደብዳቤውን ግልባጭ ለቦርዱ ይልካል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ከቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በተገለጸለት መሠረት ድርጅቱ ወይም ተቋሙ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የፈቃድ ጥያቄውን ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ይህንኑ ለቦርዱ ያሳውቃል፤ የቦርዱ ውሳኔ እስኪደርሰው ድረስ ድርጅቱ የማስተማር

ስራውን በጊዜያዊነት እንዲያቋርጥ ሊያዘው ይችላል። ድርጅቱ የማስተማር ተግባሩን ያላቋረጠ ከሆነ ጽ/ቤቱ በአካባቢው ላለ የሲቪል ማህበራት ምዝገባ ፅ/ቤት ወይም የሲቪል ማህበሩን ለመዘገበው ወይም ለሌላ ለሚመለከተው የመንግስት ተቋም ያሳውቃል።

3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመራጮች ትምህርት የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለቦርዱ መረጃ ያቀርባል። ነገር ግን የተከሰተው ችግር አስቸኳይ መፍትሔ የሚያስፈልገው ከሆነ ችግሩ እንደተከሰተ ወዲያውኑ ተገቢውን መረጃ ለቦርዱ መላክ አለበት፤ ቦርዱ ከደረሰው መረጃ በመነሳት በመራጮች ትምህርት ዙሪያ የተፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ በየወቅቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወስዳል።

## አንቀጽ 7. የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ስለመጠየቅ

1. በምርጫ ህጉ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የመራጮች ትምህርት የማስተማር መስፈርትን የሚያሟላ ማንኛውም ሀገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም የትምህርት ተቋም፡-

   ሀ) ቦርዱ ለዚሁ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና ማስረጃዎቹን በማያያዝ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

   ለ) የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የመደበውን የገንዘብ መጠን ፣ የሚያስተምርበትን ቋንቋ ፣ ለምን ያህል ዜጎች ትምህርቱን ለመስጠት እንዳቀደ፣ የሰው ኃይል አመዳደቡን፣ እና የማስተማር ሥራውን የሚያካሂድበትን ክልል፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ያካተተ ሰነድ በማዘጋጀት ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

ሐ) ለመራጮች ትምህርት በመሪነት፣ በአስተባባሪነት፣ እና በመሳሰሉ ተግባራት የሚያሠማራቸውን ሰዎች ዝርዝር ፣ እንዲሁም እነዚሁ ግለሰቦች የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆኑ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሃላፊ የተፈረመ ቃለ መሃላ ፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት ቦርዱ ባዘጋጀው ቅጽ የተሟላ የአሰልጣኞች ዝርዝር(ለገጽ ለገጽ ስልጠና ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን) እንዲሁም ተያያዥ ማስረጃዎችን አባሪ በማድረግ ከማስተማር ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

መ) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) እስከ 1(ሐ) የተደነገጉት ቢኖሩም ድርጅቱ ወይም ተቋሙ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮና በሌሎች የሚዲያ አውታሮች ብቻ ለሚሰጠው ትምህርት ወይም ትምህርቱን የሚሰጠው ሙሉ በሙሉ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮና በሌሎች የሚዲያ አውታሮች ብቻ ከሆነ የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የመደበውን የገንዘብ መጠን፣ትምህርቱን ለማስተላለፍ የሚጠቀምበትን ቋንቋ እና በዚህ ንኡስ አንቀጽ ውስጥ በተጠቀሱት የመገናኛ ብዙሃን በመጠቀም ሊያቀርብ ያቀደውን ትምህርትና ያቀራረብ ዘዴ የሚያሳይ ሰነድ ከማመልከቻው ጋር ማቅረብ አለበት።

2. የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ከቦርዱ ፈቃድ የሚጠይቅ ሀገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በህጋዊነት ተመዝግቦ በስራ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በድርጅቱ ዋና ኃላፊ ፊርማ እና በድርጅቱ ማህተም ተረጋግጦ መቅረብ አለበት።
4. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመራጮች ትምህርት ፈቃድ የመስጠት ሃላፊነትን ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊሰጥ ይችላል።

**አንቀጽ 8. ስለፈቃድ አሠጣጥ**

1. ቦርዱ የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት፡-
   ሀ) በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በምርጫና ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚሰራና በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም የትምህርት ተቋም መሆኑን፤
   ለ) በዚህ መመሪያ ለመራጮች ትምህርት የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን፣
   ሐ) ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን፤
   መ) ድርጅቱ፣ የድርጅቱ መሪም ሆነች በድርጅቱ የተመደበችው አሰልጣኝ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነች መሆኑን በማጣራትና ቦርዱ ያዘጋጀውን የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሥነ ምግባር መመሪያ ስለመቀበላቸው ድርጅቱንና አሰልጣኞቹን በማስፈረም የማስተማር ፈቃድና የአሰልጣኝ መለያ መታወቂያ ይሰጣል።

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ለማያሟላ ድርጀት ፈቃድ አይሰጥም ። አለመፍቀዱንም ከነምክንያቱ በጽሑፍ ለአመልካች ያሳውቃል።
3. የመራጮች ትምህርት የሚሰጥ ድርጅት ወይም ተቋም ከፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ወገንተኝነትን ከሚያመላክት ማንኛውም ምንጭ ወይም ከሕገ ወጥ ምንጭ ገንዘብ በመቀበል ለመራጮች ትምህርት ማዋል የለበትም።
4. የመራጮች ትምህርት የሚሰጥ ተቋም የመራጮች ትምህርት ዕቅድ እና የማስተማሪያ ቁሳቁስ አዘጋጅቶ ቦርዱ ባፀደቀው የመራጮች ትምህርት ማኑዋል መሠረት ሥራ ላይ ማዋል አለበት።

**አንቀጽ 9. የመራጮች ትምህርት አሰልጣኝ**

1. ማንኛዋም የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የምትሰማራ አሰልጣኝ፡-
   ሀ) እድሜዋ 21 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣
   ለ) የመምረጥና የመመረጥ መብቷ በህግ ያልተገደበ፣

ሐ) ተግባሯን ለመፈፀም ሙያዊ ብቃት፣ ልምድና ከመራጮች ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የትምህርት መስኮች ዝግጅት ያላት፣

መ) የምታስተምርበትን አካባቢ ቋንቋ የምትችል፣

ሠ) ቀደም ሲል የመራጮች ትምህርት ከማስተማር ጋር በተያያዘ በቦርዱ ያልታገደች ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባት መሆን አለባት።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(መ) የተነገረው ቢኖርም የመራጮች ትምህርት የሚሰጥበትን የአካባቢ ቋንቋ የምትችል አሰልጣኝ በማትገኝበት አካባቢ ትምህርቱ በአስተርጓሚ እገዛ እንዲሰጥ ቦርዱ ሊፈቅድ ይችላል።
3. ማንኛውም የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ድርጅትም ሆነ አሰልጣኝ ከስነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ/ስትንቀሳቀስ ከተገኘ/ች ቦርዱ እንደአግባብነቱ ለግለሰቧም ሆነ ለወከላት ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱ እንዲታረም ለማድረግ ወይም ፈቃድ እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

## አንቀጽ 10. አሰልጣኞችን ስለማሳወቅ

ማንኛውም የመራጮች ትምህርትን ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት የገጽ ለገጽ ትምህርት የሚሰጥ ከሆነ፡-

1. የመራጮች ትምህርት የሚሰጡላት አሰልጣኞች ይኖሩታል፤ የአሰልጣኞቹንም ማንነት ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።
2. ድርጅቱ የአሰልጣኞቹን ዝርዝር ለማሳወቅ የሚጠቀመው ቅፅ በቦርዱ የተዘጋጀ ይሆናል።

## አንቀጽ 11. አሰልጣኝ ስለመለወጥ

ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ገጽ ለገጽ ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት አሰልጣኙን ሲለውጥ በ7 ቀናት ውስጥ የሚተካውን ሰው ለቦርዱ በማሳወቅ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።

**አንቀጽ 12. የማስተማር ፈቃድ እና መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት**

1. ቦርዱ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 125 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በዚህ መመርያ መሠረት ፈቃድ ለሰጠው ድርጅት የማስተማር ፈቃድ እና አሰልጣኝ ካለው ለአሰልጣኟ መለያ መታወቂያ ካርድ ይሰጣል።
2. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድም ሆነ የመታወቂያ ካርድ አገልግሎት የሚሰጠው ለአንድ የምርጫ ወቅት ብቻ ይሆናል።

**አንቀጽ 13. የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ**

1. ቦርዱ ለመራጮች ትምህርት የሚሆን የፅሁፍ፣ የምስል ወይም የድምፅ እና የመሳሰሉትን ማስተማሪያዎች በማዘጋጀት ወይም በሌላ ሰው እንዲዘጋጅ በማድረግ ወይም ሌላ ሰው አዘጋጅቶ የሚሰጠውን ጽሁፍ፣ ድምፅ ወይም ምስል ይዘት እና ብቃት በማረጋገጥ ለማስተማሪያነት እንዲውል ሊያደርግ ይችላል።
2. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም የሚከተለውን የትምህርት አሰጣጥ በስራ ላይ ሊያውል ይችላል፣
   ሀ) የገፅ ለገፅ ስልጠና ለሚመለከታቸው አካላት ወይም ሰዎች አዘጋጅቶ መስጠት፣ እና/ወይም ፣
   ለ) የተለያየ የማስተማሪያ ፅሁፍ፣ ምስል፣ ድራማና የመሳሰለውን በማዘጋጀት እና እንዲዘጋጅ በማድረግ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በፖስተር፣ በቢልቦርድ፣ በበራሪ ጽሁፍ፣ በኢንተርኔት አውታሮች እና በመሳሰሉ መገናኛዎች እንዲወጣ ማድረግ።
3. አንድ የማስተማሪያ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሠረት የተመለከቱትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን መከታተል የሚያስችለው የአሰራር ስርአት ይዘረጋል ። አስፈላጊ ሲሆንም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል። ቦርዱም ይህንን ክትትል የሚያደርግበት ማንዋል ወደፊት የሚያወጣ ይሆናል ።
4. ቦርዱ የመራጮች ትምህርትና የመሳሰሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በማዘጋጀት ወይም በመተርጎም መራጩ ስለምርጫ እንቅስቃሴ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያደርጋል።

5. አንድ የማስተማሪያ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም የሚሰጠው የመራጮች ትምህርት በመምረጥም ሆነ በመመረጥ እንዲሁም ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመጠቀም ሴቶች ከወንዶች እኩል በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠ መብት ያላቸው መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ ማስተማር ይኖርበታል፤ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ወይም የሚያሰማራቸው አሰልጣኞች የሚጠቀሟቸው ማናቸውም የማስተማሪያ ዘዴዎችም ሆነ ቋንቋዎች፣ ሰነዶችና ቁሳቁሶች የሴቶችን እኩልነት የሚያጎለብቱ፤ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበረውን የተዛባ አመለካከት የማያንጸባርቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተነገረው ግዴታ አካል ጉዳተኝነትን በሚመለከትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
7. ማንኛውም በምርጫ ህጉ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት ቦርዱ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የመራጮች ትምህርት የሚሰጥ ድርጅት ወይም ተቋም ለቦርዱ ባቀረበው የማስተማር እቅድ እና በቦርዱ በተዘጋጁ ወይም ተቀባይነት ባገኙ ሰነዶች ይዘት መሠረት ማስተማር አለበት።
8. ማንኛውም ድርጅት ወይም ተቋም በቦርዱ ከተዘጋጀው ውጪ የማስተማሪያ ሰነድ የሚገለገል ከሆነ በቦርዱ ከተዘጋጁ ሰነዶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 14. የመራጮች ትምህርት ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች

1. ቦርዱ የመራጮች ትምህርት የሰልጣኞችን የትምህርት ደረጃና ሌሎች ተገማች ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት እንዲዘጋጅ ያደርጋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ለመራጩ ህዝብ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ለምርጫ ታዛቢዎች፣ ለጋዜጠኞች፣ በሀገሪቱ ህግ መሠረት ተመዝግበው ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለመንግስታዊ ድርጅቶች፣ ለሙያ ማህበራትና ለሕዝባዊ ድርጅቶች ምርጫን እና መራጮችን የሚመለከት ትምህርት ይሰጣል ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት በሌላ በህግ አግባብ በተፈቀደለት ድርጅት እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች መከተል ስለሚኖርባቸው ስነምግባር

### አንቀጽ 15. የማስተማር ኃላፊነትን በተገቢው መንገድ ማከናወን

ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወይም ድርጅቱ ያሰማራት አሰልጣኝ፡-

ሀ) በመራጭነት የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ማንኛውም ዜጋ የመምረጥ መብቱን እንዲጠቀም ፣

ለ) መራጮች በፖለቲካ ፓርቲዎችና በእጩዎች የሚደረጉ የምርጫ ቅስቀሳዎችን በንቃት እንዲከታተሉ እንዲሁም የሚቀርቡ አማራጭ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን እንዲረዱ አስፈላጊ ከሆነም ማብራሪያ የመጠየቅ መብት እንዳላቸው፣

ሐ) መራጮች የሚቀርቡ አማራጭ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በጥንቃቄ ከተረዱ በኋላ ለሚፈልጉት የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጡ፣

መ) መራጮች ሕግን ማክበር እና ግጭትን ከሚቀሰቅሱ ወይም ሰላምን ከሚያደፈርሱ ድርጊቶች መቆጠብ እንዳለባቸው ማስተማር አለበት/አለባት፡፡

### አንቀጽ 16. ገለልተኛ ስለመሆን

1. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወይም ድርጅቱ ያሰማራት አሰልጣኝ፡-

ሀ) ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆን አለበት/አለባት፣

ለ) ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ከመወገን፣ በመቃወም ወይም በመንቀፍ መንቀሳቀስ የለበትም/የለባትም፤

ሐ) ማንኛውም ሌላ ሰው አንዱን እንዲደግፍ ሌላውን እንዲቃወም፣ እንዲነቅፍ ወይም እንዲያጥላላ መቀስቀስ የለበትም/የለባትም፡፡

2. ማንኛውም የመራጮችን ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወይም አሰልጣኝ ፡-
   ሀ) በምርጫ እንቅስቃሴ የሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅትን፣ የእጩዋን ወይም የግል እጩን ማንኛውንም አይነት ደጋፊ ወይም ተቃራኒ ምልክት፣ መፈክር፣ ወይም የመሳሰለውን በመለጠፍ፣ በመስቀል፣ በማውለብለብ ወይም በማንኛውም መልኩ ይዞ መገኘት የለባትም።
   ለ) እየተካሄደ ባለ ምርጫ ላይ የግል አስተያየት ከመስጠት የመቆጠብ ግዴታ አለባት።
   ሐ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የምትደግፈውን ፓርቲ ወይም እጩ በአደባባይ መግለጽም ሆነ ደጋፊነቷን የሚያስጠረጥር ድርጊት መፈጸም የለባትም፤
   መ) ፍጹም ገለልተኛ የመራጮች ትምህርት የመስጠት ግዴታ አለባት።

**አንቀጽ 18. የጥቅም ግጭት**

1. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ፈቃድ የወሰደ ሀገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም ተቋም በንብረት፣ በገንዘብ፣ በዝምድና ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ከምርጫ ተወዳዳሪ እጩ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ጋር የጥቅም ግንኙነት ሲያጋጥመው ጉዳዩን ዘርዝሮ ወዲያውኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።
2. ቦርዱ የጥቅም ግጭት ያጋጠመው ሰው ሪፖርት ሲደርሰው በሌላ አካባቢ እንድታስተምር፣ ማስተማሯን እንድትቀጥል ወይም ሌላ አስፈላጊ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**አንቀጽ 19. እውነተኝነት**

ማንኛውም በምርጫ ህጉ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ደርጀት ወይም ተቋም ወይም አሰልጣኝ፡-

1. በማንኛውም ጊዜ የምታስተምረው የመራጮች ትምህርት፣ የምታሰራጨው መረጃ፣ ወይም ለቦርዱ የምታቀርበው ሪፖርት በእውነተኛ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለበት።

2. የምታስተምረው የመራጮች ትምህርት ዝግጅት፣ ዕቅድ እና የትምህርት አሠጣጥ ቦርዱ ባፀደቀው የትምህርት ይዘትና ቅደም ተከተል እና የምርጫ ዑደት መሠረት መሆን ይኖርበታል። ይህንን የሚቀይር ከሆነ የቦርዱን ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21(3) መሰረት ለመራጮች ትምህርት ከቦርዱ የገንዘብ ድጋፍ ያገኘ ከሆነ ገንዘቡን ለታቀደለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለበት።

## አንቀጽ 20. ህግ ማክበር

1. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት የማስተማር ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ድርጅቱ የመደባት አሰልጣኝ ህገ መንግሥቱን፣ የምርጫ ህጉን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች እንዲሁም በዚህ ስነምግባር መመሪያ የገባችውን ግዴታ ማክበር አለባት።
2. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ደርጅት ወይም አሰልጣኝ በዚህ መመሪያ ከገባው የስነ ምግባር ግዴታ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደየሁኔታው፤
   ሀ) ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ፣ ወይም
   ለ) የማስተማር ፈቃድ እና የአሰልጣኝ መታወቂያ ወረቀትን እስከመሰረዝ ሊደርስ የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይችላል።
3. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ደርጅት ወይም ተቋም
   ሀ) የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የተሰጠውን የተረጋገጠ የፈቃድ ቅጂ እና መለያ መታወቂያ የመያዝ እና አግባብ ባለው ሰው ሲጠየቅም ማሳየት፣
   ለ) በህግ መሠረት ብቻ የማስተማር፣
   ሐ) የምርጫ ሂደት በትክክል እንዳይካሄድ ከሚያደርግ እንቅስቃሴ እና ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ ከመንቀሳቀስ የመቆጠብ፣
   መ) በዚህ መመሪያ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት።

4. ፍቃድ የተሰጠው ድርጅት የመደበት አሰልጣኝ ህገወጥ ድርጊት በመፈፀሟ ወይም ይህንን መመርያ በመጣሷ ምክንያት ቦርዱ ማስጠንቀቂያ የሰጣት እንደሆነ አፋጣኝ ማስተካከያ በመውሰድ ለቦርዱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 21. የገንዘብ ምንጭ

1. ማንኛውም ደርጅት ወይም ተቋም የመራጮች ትምህርት ማካሄጃ ወጪን በራሱ ይሸፍናል።
2. የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ድርጅቶች ወይም ተቋማት ለዚሁ ተግባር የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ለሚያደርጓቸው ጥረቶች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ቦርዱ የድጋፍ ደብደቤ ሊጽፍላቸው ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የተደራሽነት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ለሚሰጠው የመራጮች ትምህርት በትብብር ለሚሰሩ ድርጅቶች ወይም ተቋማት በስምምነት ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 22. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. ማንኛውም የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ፦

   ሀ. ማስተማሩን እንዳጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ ክንውን ሪፖርትን እና በቦርዱ የሚጠየቁ ተገቢ ሰነዶችን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

   ለ. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

   ሐ. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (ለ) ከተጠቀሱት ሪፖርቶች ጋር እንቅስቃሴውን የሚያሳይ በፅሁፍ ፣ የቪዲዮ ፣ የምስል እና የድምፅ ሰነዶችን በአባሪ ማስረጃነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

   መ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም ጊዜ በቦርዱ ሲጠየቅ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21(3) መሰረት የገንዘብ ድጋፍ ከቦርዱ የሚያገኝ ድርጅት ወይም ተቋም ከሚያቀርበው የስራ ክንውን ሪፖርት ጋር የተሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 23. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 24. ቅጣት**

በዚህ መመሪያ የተደነገገውን የስነምግባር ግዴታ ያልፈፀመ ወይም የጣሰ ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 25. ማኑዋል ስለማውጣት**

ቦርዱ ይህንን የስነምግባር መመሪያ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የአፈጻጸም ማኑዋል ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 26. የተሻሩ ህጎች እና አሠራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 27. የተፈጻሚነት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ